# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ጥር 2002

## ለኢትዮጵያ ወጣቶች በሞላ ሀገር አድን ጥሪ፤

**የውድ ኢትዮጵያ ወጣቶች ሆይ፤**

**እናት ሀገራችን ኢትዮጵያ ዛሬ ህልውናዋ ከመቸውም ይበልጥ ለከፋ አደጋ ተጋልጦ ይገኛል። በጀግና ልጆቿ ደም ታፍራና ተከብራ ያልቆየች ይመስል ዛሬ ከመሀሏ በበቀለ ሙኛ እጅ እግሯ ተይዞ ለጠላት ተዳርጋለች። የሀገራችን መሬት ለሱዳን ተሰጥቶ የባዕድ ጦር በሀገራችን መሬት ሰፍሯል። የሀገራችን ለም መሬት ለባዕዳን በገፍ እየተሸጠ ኢትዮጵያውያን በገዛ ሀገራቸው ለዘመናዊ ቅኝ አገዛዝና የረቀቀ ብዝበዛ እየተዳረጉ ናቸው። ብዙ መቶ ሺ ወጣቶች በትምህርት ገበያ ላይ ሊገኙ ሲገባ ለመንገድ አዳሪነት ተዳርገዋል፤ ሚሊዮኖች ሥራ አጥ ሆነዋል፤ ብዙ ሺዎች ለጦርነት ተማግደው ለባዕድ ጥቅም ሲባል ውድ ህይወታቸው አልፏል። ረሀብና የኑሮ ውድነት ለጋ ህይወትን ለስቃይና ለሞት እየዳረገ ነው። ወጣት ሴቶች ለሴተኛ አዳሪነትና ለዘመናዊ ባርነት ሲዳረጉ ወጣቱ በአጠቃላይም ለጎጂ ልምዶችና ቀሳፊ በሽታዎች ሰለባ ሆኗል። ከሁሉም በላይ አስከፊ የሆነው ደግሞ ወጣቱ በብሔረሰብና በሃይማኖት ደረጃ በመሰሪዎቹና ዘረኞቹ መከፋፈሉ ነው።**

**የኢትዮጵያ ወጣቶች ሆይ!**

**ሀገራችንን ኢትዮጵያ ከወያኔ መንጋ ለማላቀቅና ህልውናዋንና ሉዓላዊነቷን ለማስጠበቅ ታሪካዊ ተጋድሎ መካሄድ እንዳለበት ግልፅ ነው። ይህ ለመጪው ትግል አይለጉት ሀኬት፤ አያስተላልፉት ግዳጅ ሆኖም ይገኛል - የዛሬ ወጣት፤ የዛሬ ትውልድ ግዳጅና ሃላፊነትም ነው። እነ ዘርዓይ ደረስ፥ ጥቁር አንበሶች፥ አብረሃም ደቦጭና አያሌው ወጣት ወንድና ሴት የጣሊያን ሙሶሊኒን ወራሪ ጦር ተጋፍጦ፤ ከሚሊዮን በላይ ህይወትም ለሀገር ደህንነት ተገብሮ ኢትዮጵያ ነፃነቷን ጠብቃና ለሌሎችም የነፃነት ቤዛና አርዓያ ሆና ቆይታለች። ኋላ ቀር ሥርዓት ሕዝብን ለድህነትና ጢሰኝነት ዳርጎ ባሰቃየበትም የኢትዮጵያ ወጣቶች በብሔረሰብ ሆነ በሃይማኖት ሳይለያዩ በጋራ በመነሳት የየካቲትን አብዮት የለውጥ መንገድ አድርገውታል። እነ ጥላሁን ግዛው፥ ማርታ መብራቱ፤ ደመቀ ዘውዴ፥ ጌታቸው፥ ዮሐንስና ሌሎችም ተሰውተዋል። ብዙዎች ተገርፈዋል፤ ለስደትም ተዳርገዋል። ያ ጀግና ለውጥ አብሳሪ ትውልድ የራሱን ምኞትና ድሎት ከመጤፍ ሳይቆጥር ለሕዝብ ታግሏል። 'ፋኖ ተሰማራ፤ በዱር በገደሉ ትግሉን ልትመራ' ብሎ ያዜመውና ለብዙሀኑ ሠርቶ አደር ሕዝብ ጥቅምና ክብር የቆመው ወጣት ሁሉ እነሆ ዛሬም እየተዘከረና እየተመሰገነ ያለ መሆኑንም መካድ የሚቻል አይደለም።**

እያንዳንዱ ትውልድና በየትውልዱ ያለ ወጣት የየራሱ ግዳጅና ግግደ መስቀል እንዳለበት የታወቀ ነው:: ያለፉት ትውልዶች ሀገርን ከጣሊያን ወረራ ማላቀቅና ቀጥሎም ጨቋኙን የአፄ ሥርዓት መገርሰስ ነበረባቸው:: የዛሬ ወጣቶች ደግሞ ሀገርን ከዘረኛና ጠባብ አረመኔ የወያኔ ቡድን ማዳን ዋናው ግዴታቸው ነው:: የትላንትናና የዛሬ የትግል ሁኔታና ይዞታ፤ የሀገርና የዓለም አቀፍ ሁኔታ የተለያዩ መሆናቸውም ሊዘነጋ የሚችል አይደለም:: ሆኖም ሀገርን ከጥፋት ማዳን የሚችለው ኃይል ወጣቱ ለመሆኑ ክርክርን አይጠይቅም:: ፋሺስታዊው ደርግ የሕዝብን ድል ነጥቆ በሥልጣን ሲሰየም ወጣቶች በኢሕአፓ ሥር ተሰልፈው ያካሄዱት ትግልና የከፈሉት መስዋዕት በታሪክ የተመዘገበና ሁሌም የሚታወስ ነው:: የታሪክ ላፒሶች ወንጀላቸውንና ሀፍረታቸውን ለመደበቅ ዛሬ ያንን ጀግና ትውልድ ሊከሱና ታሪኩን ሊያጠፉ ቢቅበዘበዙም አልደበቅ ያለው ሐቅ ወጣቱ ትውልድ የወደቀበትን ግዳጅ ተቀብሎ ሀገር የጠየቀችውን ከባድ መስዋዕትነት መክፈሉ ነው:: የሰማዕቱ ስም ዝርዝር በመቶ ሺዎች ሲዘረዘር ገድላቸው ደግሞ ለመጪው ትውልድ ሁሉ አርዓያ ሆኖ ይገኛል:: የተጋፈጡት ወታደራዊ አገዛዝ ሰው በላና አረመኔ ነበር--የዛሬዎቹም አረመኔና ሀገር አጥፊ ናቸው:: የትላንቱ ኃያል ነኝ የማልበገር ብሎ በትዕቢት ተወጥሮ ነበር--የዛሬውም በዘረኛ ጦሩና የአፈና ተቋሙ ይኩራራል:: የዛሬው ዓለም አቀፍ ሁኔታ አንድ ኃያል መንግሥትን ያሰፈነ በመሆኑና ይህም ኃይል ከአረመኔው ወያኔ ጋር ማበሩ ሁኔታውን ለወጥ ከሚያደርጉት ክስተቶች አንዱ ሆኖም ይታያል::

የኢትዮጵያ ወጣቶች ሆይ!

ላይችል አይሰጠውም ነውናም ለዛሬ ችግሮችና እንቀፋቶች ሁሉ ወጣቱ ትውልድ መፍትሄ መሻትና ማግኘትም እንደሚችል ቅንጣትም ጥርጣሬ ሊኖራችሁ አይገባም:: ትላንት ወጣቶች በኢትዮጵያዊነታቸው የተባበሩ ቢሆኑም ከመሀላቸው ያኔም ብቅ ያሉ ዘረኛ እንክርዳዶች ነበሩ:: እነዚህ ግን በትግል ተሸናፊ ሆነው የበላይነትን ሊይዙ አልቻሉም ነበር:: ዛሬ ዘረኛው ቡድን ዋና ፖለቲካው ሕዝብን በብሔረሰብና በሃይማኖት መከፋፈል በመሆኑ በተለይ የራሱን ብሔረሰብ ወጣቶች ከሌሎች አቃርኖ ይኖራል:: መሰል ጠባቦችም የወጣቱን አንድነት እየተፈታተኑት ናቸው:: ወጣቶች ግን ይህን ዘረኛ አገዛዝ መታገላችሁ መቸም መዘንጋት የለበትም:: ለሥልጣን ሲበቃ ጀምሮ እስከ 1997-ኡ ምርጫ ድረስ የብዙ ወጣቶች ደም በፀረ-ወያኔ ትግል አልፏል:: በየእስር ቤቱ እየተሰቃየ ያለው ወጣቱ ነው:: አደገኛ ቦዘኔ እየተባለ የህሊናና የአካል ስየል በመቀበል ላይ ያለው ወጣቱ ነው:: ለአረብ ሀገሮች ለዘመናዊ ባርነት የተሸጡት ወጣቶች ናቸው:: ለጦርነት ከባድሜ እስከ ሞቃዲሾ ተዳርገው ሰለባ የሆኑት ወጣቶች ናቸው:: ይህ በወጣቱ ላይ ያተኮረ መዓት ማጠየቂያው ለሀገር ህልውና ሊታገል የሚችለውን ወጣት ክፍል ለመበታተንና ለማጥቃት መሆኑ መታወቅ ያለበት ነው:: ወጣቱ በጎጂ ባህሎች እንዲጠመድ ሁኔታው የሚመቻቸውም ለዚሁ ነው:: የኢትዮጵያ ወጣቶች ይህን ማወቅ አለባቸው::

አንድ ትውልድ ታጋይ ሌላው ትውልድ ቡከንና ህሊና ቢስ ነው የሚል ድምዳሜ ከሐቅ ከመጣላቱ ሌላ ጠቀሜታው ለመሰሪው ወያኔ መሆኑ መታወቅ አለበት:: ያለፈው ትውልድ አኩሪ



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel . 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

የትግል ታሪክ ፅፎ እንዳለፈው ሁሉ የዛሬውም ወጣት ትውልድ አስደናቂ የጀግንነት ገፆችን ፅፎ ማለፉ የማይቀር መሆኑ መታወቅ አለበት። ያለፈው ትውልድ የሚያታግለውና ቆራጥ የሚያደርገው የትግል ድርጅት ነበረው። በ1997 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ወጣቶችም መሪ ካገኙ መስዋዕትነትን እንደማይሸሹ ደማቸውን ከፍለው አሳይተዋል። መሪ ነን ያሉት ተፍረከረኩ እንጂ ወጣቶች አልሸሹም። በዚያን ወቅትም የክፍፍልና ዘረኛ ጎጦች ጨልመው እንደነበር የምንረሳው አይደለም። ስለዚህም የኢትዮጵያ ወጣት የዘረኛውን ቡድን በብሔረሰብና በሃይማኖት ከፋፋይ ወጠመድ በጣጥሶና ኢትዮጵያዊ አንድነቱን አጠናክሮ ሊታገል ይችላል። የወያኔ አገዛዝ ዛሬም ወጣቱን ለጦርነት ሊዳርግ ኑ ተመልመሉ፤ ወታደርነት ተቀጠሩ አያለ ነው። ወጣቱ ከእንግዲህ ወዲህ ለአድህሪና ፀረ-ኢትዮጵያ አገዛዝ ጭዳ አንሆንም ማለት ይጠበቅበታል። ከእንግዲህ ደማችን የሚፈሰው ሀገራችንን ከወያኔ ጥፋት ለማዳን ነው ብሎ በጋራ እንዲቆም ያስፈልጋል።

የኢትዮጵያ ወጣቶች ሆይ፤ በገጠር በከተማ ያላችሁ ወጣቶች ሆይ!

የወሳኝ ትግል ደወል አቃጭሏል-- ሀገር አድን ግዳጅ የዛሬ እንጂ የተነገ ወዲያ አይደለም። ለሀገር አድኑ ትግል መነሳት መንሳሳት ይጠበቅባችኋል። ድል የምትወለደው ከወያኔ የምርጫ ሳጥን ሳይሆን በዱር በገደሉና በከተሞች ከሚያስተጋባ ፀረ-ወያኔ ትግል ብቻ ነው። ለዚህ ትግል ተዘጋጁ። የተወረረችና ለባዕድ የተሰጠችን ሀገር ለማዳን ተጨባጭ ድርጊቶችን መውሰድና ጠላትን መቅጣት ያስፈልጋል። መቅጫው ደግሞ በደጃችን አለ -- በስልትና በቆራጥ እርምጃዎች በእጃችን ልናስገባው እንችላለን። በየካቲት 66ና ከዚያም በኋላ በከተሞችና በገጠር ከተካሄዱት ትግሎች ብዙ መማር እንችላለን። በዕብሪት የተወጠረውና ውስጡ ግን ወንፊት ሆኖ እየመጣ ያለውን የወያኔ አገዛዝ ማዋከብና ማሸበር ብሎም ማቸነፍ እንችላለን። ተባብረን ከታገልን ኃይሌ ያለው ይፈርሳል፤ የባዕድ እርዳታም ከሕዝብ ቁጣና ቅጣት አያድነውም። ሕዝባዊ ትግሉ ይሰምር ዘንድ ግን አብዛኛው ሕዝብ በትግሉ መሳተፍ አለበት። ዛሬ ከኢትዮጵያ ሕዝብ አብዛኛው ወጣት ነውናም ወጣቱ ለትግል መነሳቱ በጣም አስፈላጊና ወሳኝ ነው። ኢሕአፓ ለዚሁ ትግልና ግዳጅ ድርጅታዊ ምላሽን ለመስጠት የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ድርጅትን (ኢሕአፓወክንድ-ን) መስርቶ በሀገርና በውጭ ያሉ ወጣቶች ተሰባስበውና ተደራጅተው እንዲታገሉ እየጣረ ነው። ወጣቶች፥ በሌላ በመሰላቸሁ ሀገር አድን መልክ መደራጀትም ትችላላችሁ። ዋናው ቁም ነገር፥ ለኢትዮጵያ ህልውና መጠበቅ በተጨባጭ መታገሉ ላይ ነው። የትግል መስኮች አሉ፤ ነገ ደግሞ ሌሎች መስኮችም ይከፈታሉ። በነዚህ አማካኝነት መታገል የሚቻል ነው። ከዚህ ባሻገር ወጣቱ በቡድን ቡድን ሆኖ፤ ጨለማንም ስልትንም ተገን አድርጎ ጠላትን ማጥቃት ይቻላል። ቆራጥነትና አፈላቂነት፤ ብልሃትና ዘዴ ከወጣቱ ጎራ ሞልቷልና በተግባር መታያቸው ጊዜ ዛሬ ነው።

የኢትዮጵያ ወጣቶች ሆይ!

ውድ ሀገራችንን ከማጣታችን በፊት በወያኔ አገዛዝ ላይ እንነሳ!
ኢትዮጵያን እናድን !



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France